# *የመጠጥ ውኃ ፍላጎትንና አቅርቦትን የማቀራረብ ሩጫ በድሬዳዋ*

*በጸጋቸው ምትኩ 11-19-17*

ፍላጎትና አቅርቦት እንደ ሩጫ በመም ላይ ነው ወይስ በጎዳና የተገናኙት የሚል ጥያቄ ቢነሳ የሚገርም አይደለም። ፍላጎትና አቅርቦት በአካል ገዝፈው ባይታዩም እነዚህ ፍላጎቶችን የሚጠይቁ ሰዎች ፣ ማህበረሶችና ህዝቦች በእሽቅድድም ላይ ሆነው ይታያሉ። እንግዲህ እነዚህን ነው ተሽቀዳዳሚ የምላቸው። ከነዚህ ፍላጎትና አቅርቦት እሽቅድድም ከሚገለፅባቸው ነገሮች አንዱ የመጠጥ ውኃ ነው። በዚህ ፅሁፍ ከከአዲስ አበባ 525 ኪሎ ሜትር የምትርቀው ድሬዳዋን የመጠጥ ውኃ አቅርቦትን የማቀራረብ ሩጫን በዝርዝር እንመለከታለን።

የከተማዋን ሙሉ ገፅታ ለማወቅ ይረዳን ዘንድ ስለድሬዳዋ ትንሽ ማለቱ ሳይበጅ አይቀርም።

ብዙ አርቲስቶች በግጥሞቻቸውና በዘፈኖቻቸው ድሬን የበረሃዋ ንግስት ያደርጓታል። ይህንን ስያሜ ያሰጣት ምናልባት ቆንጃጅቶቿና ሙቀቷ ይሆናል የሚል መላ ምት ይሰጣል። ባይኑ ላዩ ለእኔ አይነቱ ሰው ደግሞ ሙቀት እና ሁለገብ ውበት አይቶ ቢባልላት አያንሳትም ሊል ይችላል። እንግዳ ተቀባዩዋ ከተማ ድሬዳዋ ከአዲስ አበባ 525 ኪሎሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች።ድሬዳዋ ከአዲስ አበባ ቀጥሎ በትልቅነቷ ተጠቃሽ ከተማ ናት ።

ከሶስት መቶ ሽህ ህዝብ በላይ ነዋሪ ያላት ድሬዳዋ በአዲስ አበባ ጅቡቲ የባቡር መስመር ላይ የምትገኝ የንግድና የኢንዱስትሪ ከተማ ናት። አመሰራረቷም ከዚሁ የባቡር መስመር ዝርጋታ ጋር በመገናኘቱ ባቡር የወለዳት ከተማም ይሏታል። ነገሩ እውነትነት አለው። ድሬዳዋ በ1902 ዓ.ም. የባቡር መስመሩ ከተማዋ ሲደርስ መመስረቷን የታሪክ ድርሳናት ያመለክታሉ።

ሌላው እድገቷና መቆርቆዟ ከባቡሩ ጋር መሆኑን የሚያመለክተውና ትልቁ ማሳያ ለረጅም ዘመናት የቆዬው የባቡር መስመሩ ስራውን ሲያቋርጥ የከተማዋ እድገት መቀዛቀዙ ነው። ዘፈኑም የተዘፈነላት ከባቡሩ ጋር የተያያዘ መሆኑ ስንቶቻችን ልብ እንደምንለው እርግጠኛ ባልሆንም እሄዳለሁ ድሬ ባቡር ተሳፍሬ የሚለውን ዘፈን ሳንሰማው የምንቀር አይመስለኝም። ሁላችንም ድሬዳዋን የምንናፍቀው ምናልባት ባቡር ተሳፍሮ ከመሄድ ጋር የተያያዘም ሊሆን ይችላል።

አሁንም የኢትዮ- ጅቡቲ ባቡር መስመር እንደገና ስራ ለመጀመር አስተዳደራዊ ኮንትራቱን የሚወስድ አካል የሁለቱ ሃገሮች እየሰሩ ባሉበት ባሁኑ ወቅት እንኳ ከተኛችበት የዕድገት ሰመመን እየተነሳች ነው የሚሉ ሰዎች ብዙ ናቸው። ባቡሩ ስራውን ሲጀምር እድገቷ የበለጠ ይጨምራል የሚል እምነት ሁላቸውም አላቸው።

ለዚህም እንደማሳያ የሚሆነው ድሮም የንግድና ኢንዱስትሪ ከተማ ብትሆንም ዛሬም ላይ የነበራት ሚና የበለጠ የሚያንቀሳቅስላት በሃገሪቱ ከሚገኙት የኢንዱስትሪ መንደሮች አንዷ የሚያደርጋትን የኢንዱስትሪ መንደር እየገነባች ነው። ከኢንዱስትሪ መንደር ጎን ለጎን የበለጠ የሚያግዛት ነባሩ የኢትዮ-ጅቡቲ መንገድ 300 ኪሎ ሜትር የሚወስደውን ጉዞ ወደ 210 ኪሎ ሜትር ዝቅ የሚያደረግ መንገድ በቻይናው መንገድ ተቋራጭ ድርጅት እየተገነባላት ነው። ይህም የከተማዋን እድገት በምን ያክል ፍጥነት ሊያሳድግ እንደሚችል መገመት አያዳግትም።

ይህንን የመሰረተ ልማት ግንባታ፣ የኢንዱስትሪ መንደርነትና የቱሪስት መዳረሻነት ብሎም በየጊዜው የመቀበል አቅሙን እያሳደገ ያለው ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ድሬ እንደሚገኝ ሁላችንም ልብ የምንለው ይመስለኛል። ለዚህ ሁሉ ግንባታና ወደ ከተማዋ ለሚተም ህዝብ አንድ ነገር ያስፈልጋቸዋል - ውኃ!

ሞቃታማና ደረቃማ የአየር ንብረት ያላት ድሬዳዋ ከላይ ለሚመጣው ወበቅ መቋቋሚያ ውኃ ያስፈልጋታል።

ምክንያቱም የብዙ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መናኸሪያ የሆነችው ድሬዳዋ ብዙ የቱሪስት መዳረሻዎች አሏት። ብዙ የቅድመ ታሪክ ስዕሎች በተለያዩ ዋሻዎች፣ በኢትዮ- ጣሊያ ወረራ ወቅት የጣሊያኖች መስጊድ በሚባል የሚታወቀው ጣሊያኖች የገነቡት መስጊድ (በአጭር ጊዜ ቆይታው ከገነባው መስጊድ አንዱ ነው)፣ በሁለተኛው የኢትዮ - ጣሊያን ጦርነት ወቅት ከኢትዮጵያ ወታደሮች ጎን ተሰልፈው የተሰው ወታደሮች አፅም ያረፈበት መቃብርና የቀድሞው የባቡር ጣቢያ የቱሪስት መዳረሻዎቿ ናቸው።

በጥንታዊው የካፊራ ገበያ የተለያዩ አለባበሶችን የለበሱ የተለያዩ ማህበረሰቦችንና ክፍሎች፣ የግመልና የአህያ ግርግርና ጋሪ ካካታ ለድሬ ልዩ መገለጫዎቿ ናቸው። (የከተማዋ አንድ ሃውልት ጋሪ መጋላ መሆኑን ልብ ይሏል) ወደ ጥንታዊው መካከለኛ ዘመን የሚወስዱ ምስል ከሳቾች ናቸው። ከዛሬ 115 ዓመት በፊት ከከተማዋ 26 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የተገነባውና በጥቅምት ወር ላይ የሚከበረው የካቶሊክ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ-ክርስቲያን አማኞች የሚሰበሰቡበት አንዱ የቱሪስት መሰብሰቢያዋ ነው።

ይህችው የንግድ ማዕከል፣ የኢንዱስትሪ መንደርና የብዙ የቱሪስት መዳረሻ የሆነችው ከተማ ያላትን የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ፀጋዎቿን በአግባቡ ከመጠቀም ጎን ለጎን የሚያስፈልጓትን መሰረተ ልማቶች ማሟላት ግድ ይላታል። ከነዚህ መሰረተ ልማቶች መካከል ደግሞ የመጠጥ ውኃ አንዱ ነው። ለኢንዱስትሪም ሆነ ለንግድ ወይም ደግሞ ለቱሪዝም የውኃ አቅርቦት ከፍላጎቱ ጋር ቢቻል ማመጣጠን ባይቻል ደግሞ ለመሰረታዊ ፍላጎት የሚሆን አቅርቦት ያስፈልጋል።

አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ማንኛውም የዓለማችን ስራዎች ሰባ ከመቶው ከውኃ ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው። ውኃ ይህን ያክል ሚና የሚጫወት ከሆነ ድሬዳዋም ለውኃ መሰረተ ልማት ቅድሚያ መስጠቷ ልክ ነው ያስብላል። እ.ኤ.አ. በ2012 የተጀመረውና ከአምስቱ የከተሞች መጠጥ ውኃ ፕሮጀክቶች አንዱ የሆነ የመጠጥ ውኃ ግንባታ ጀምራለች። 700 ሚሊዮን ብር በሚጠጋ ገንዘብ የተጀመረውና በዓለም ባንክ በተለይም በዓለም አቀፉ የልማት ድርጅት በተገኘ ገንዘብ የተጀመረው ይህ የመጠጥ ውኃ ፕሮጀክት እ.ኤ.አ. በ2030 ዓ/ም ድረስ አሁን ያለውን ህዝብ እጥፍ ያክል ህዝብ ታሳቢ ያደረገ ነው። እንደሚታወቀው አሁን ያለው የድሬዳዋ ህዝብ ቁጥር ሶሰት መቶ ሽህ የሚገመት ሲሆን እስከ እ.ኤ.አ. 2030 ድረስ ስድስት መቶ ሺህ ይሆናል የሚል ታሳቢ ያደረገ ፕሮጀክት ነው።

በቅርቡ በሚደረግ የህዝብና የቤት ቆጠራ የምናገኘው ቢሆንም የድሬዳዋ ህዝብ ሃምሳ በመቶ በማደግ ላይ ነው። የህዝብ ቁጥር ሲጨምር ፍላጎቱም ይጨምራል ባለበትም አይቆምም። ለዚህ የህዘብ ቁጥርና ፍላጎት መጨመር የሚመጥን የውኃ አቅርቦት መኖር አሌ የማይባል እውነታ ነው።

በሌላ በኩል ህዝቡ በምን ያክል ፍጥነት ቢያድግ በዚህ ዓመታት ውስጥ ራሱን በእጥፍ ቢያሳድግ የሚችለው የሚል ሃሳብ ሊነሳ ይችላል። የህዝብ ቁጥር ሊጨምርባቸው ከሚችልባቸው ምክንያቶች አንዱ የከተማ መስፋፋት፣የኢንዱስትሪ መስፋፋት፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ።

በዚህም የተነሳ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ውኃና ፍሳሽ ባለስልጣን በኢፌድሪ ውኃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ስር በተቋቋመውና ዓላማውንም የውኃ መሰረተ ልማቶችን ለማሳደግ ገንዘብ ማፈላለግ አዋጪ ፕሮጀክቶችን ለሚያቀርቡ ፈንድ ከተለያየ ድርጅቶች ፈልጎ ከሚያቀርበው ከውኃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት ባገኘው የብድር ገንዘብ ግንባታውን ካካሄደ በኋላ ወጪውን በሂደት በሚሰበሰቡት የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍሉ በማድረግ ሌሎች የውኃ መሰረተ ልማቶች እንዲገነቡላቸው ለሚፈልጉ ከተሞች የማድረስ ስራ የሚሰራው ነው።

አቶ ንጉሱ መንግስቴ በድሬዳዋ ከተማ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የግዢ ባለሙያ የሚያረጋግጡትም ይህንኑ ነው። ይህ ፕሮጀክት መጪውን ጊዜ አሻግሮ ያየና መጻዒ ፍላጎቱን ታሳቢ ያደረገ ቢመስልም በአካባቢው በተዘረጉ እንደ ቴሌኮምንኬሽን፣ መብራት ኃይል፣የውኃ መስመሩ በተዘረጋባቸው አካባቢዎች መኖሪያቸውን ባደረጉ የህብረተሰብ ክፍሎች የካሳ ይገባኛል ና በፍቃደኝነት ለተነሱትም በቂ ካሳ እስከሚያገኙና እስከሚሰፍሩ ድረስ በወሰደው ጊዜ የተጓተተ ቢሆንም አሁን ባሉበት ፍጥነት ከቀጠሉ ከመጪው ችግራቸው የሚታደጋቸው ይመስላል።



ስዕል1፡- ከውሃ ሪሰርቨየሮች አንዱ

በሌላ በኩል እንደ አቶ ንጉሱ ገለፃ ከሆነ  ይህን ሁሉ አልፈው በተጫራቾች የጨረታ ሂደት  ሌላም ችግር ገጥሟቸው እሱም በግንባታው ሂደት መጓተት ሂደት ላይ የራሱን አሉታዊ ሚና ተጫውቷል ይላሉ ባለሙያው።

በግንባታው ሂደት ሶስት ስራዎች እንደሚሰሩ አቶ ንጉሱ መንግስቴ ይገልፃሉ።  ዋና ዋናዎቹም የሲቪል፣ የኤሌክትሮና ሜካኒካል ስራዎች መሆናቸውን  ያብራራሉ ። እነዚህም ስራዎች ከኤሌክትሮ ሜካኒካል  ስራው በስተቀር በመጠናቀቅ ላይ ነው ሲሉ ያስረዳሉ ። ኤሌክትሮ ሜካኒካል ስራዎች ግን ኤል. ሲ ተከፍቷል ፤በቅርቡም  ግዥ ይፈፀማል የሚል  እምነት አላቸው ባለሙያው።

የጉድጓድና ሪዘርቪየር ግንባታ ተጠናቋል።መዘርጋት ካለበት 94 ኪሎሜትር የውስጥ ለውስጥ መስመር 64 ኪሎ ሜትር ተዘርግቷል። ከስራዎች ሁሉ ዝርጋታው ብዙ ውጣ ውረዶችን  እንዲያልፉ ያደረጋቸው መሆኑን  ባለሙያው አልሸሸጉም።

የድሬዳዋ መጠጥ ውኃ ፕሮጀክት የአምስቱ ከተሞች  ፕሮጀክቶች አካል ነው። ፕሮጀክቱ  እንደ ጎርጎሮሳውያን ቀን አቆጣጠር በ2012  ተጀመሮ በ2013 ይጠናቀቃል ተብሎ የጊዜ ገደብ ቢቀመጥለትም  እንደታሰበው ግን በወቅቱ ሊሳካ አልቻለም። እስከ 2017 እንደ አውሮፓውያን የቀን አቆጣጠር ድረስ  የገንዘብ ምንጩ የዓለም ባንክ  ለሁለት ጊዜ አራዝሞት እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር   ዲሴምበር 31/2017 (ጥር 1 /2010 ዓ/ም መሆኑ ነው)  ላይ ይጠናቀቃል የሚል የጊዜ ገደብ ተቀምጦለታል።

ይህም ማለት ባንኩ ይጠናቀቅበታል  ከተባለው  ጊዜ ሁለቴ መራዘሙን  የፕሮጀክቱ ዳራ እና ባለሙያው ያረጋግጣሉ።

መስመሩ በሚያልፍበት አካባቢ  ያሉ የህረተሰብ ክፍሎችን   ማንሳት፣ የኮንትራክተሩ አቅም ማነስ ፣ የፕሮጀክቱ ማኔጀር አትኩሮት ማጣትና በግዥ ሂደት  በተጫራቾቹ አድሎአዊ አሰራር ተሰርቶብኛል የሚል እስከ ፌዴራል ፀረ- ሙስናና ስነምግባር ኮሚሽን  የደረሰ  ቅሬታ መነሳት  የገጠሟቸው ችግሮች ቢሆኑም   ተራ በተራ በመፍታት   ሂደት ውስጥ   የከተማዋ አስተዳደር ከፍተኛ ሚና እንደተጫወተ አቶ ንጉሱ አጫውተውናል።

አቶ ንጉሱ መንግስቴ እንዴት ተፈታ ላልናቸው የሚከተለውን ምላሽ ተሰጥተውናል። <<የውኃ መስመሩ በሚያልፍባቸውና ግንባታ በሚካሄድባቸው አካባቢዎች ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን  መሰረተ ልማት በማሟላት ና በማንሳቱ ድርሻ የወሰደው የከተማ አስተዳደሩ ነው።  የኮንትራክተሩን  የፋይናንስ አቅም በማጎልበት በኩልም ቢሆን  ዝግ ሂሳብ  በመክፈት  ለስራ ብቻ በሚያገለግል አኳሁዋን  ስራ በመስራትም  ቢሆን  የከተማ አስተዳደሩ ያበረከተው አስተዋፅኦ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። እንዲያውም ያንበሳውን ድርሻ ይወስዳል>> ሲሉ የተሰጠውን ትኩረት ይገልጻሉ። የኮንትራክተሩ ማኔጀር የሚጠበቅበትን  ስራ ባለመስራቱ በኩል ግን ከተቋራጩ ጋር  በመነጋገር  እንዲቀየርና የተሻለ ማኔጀር እንዲኖረው መደረጉን ባለሙያው ነግረውናል።

ከአቶ ንጉሱ ጋር በነበረን የመስክ ምልከታ አሁን በማገልገል ላይ ያለው  የውሃ ጉድጓድ ና ውሃ መጠራቀሚያ ከዛሬ ሰላሳ ዓመት በፊት ሲያገለግል የነበረው ነባሩን የውኃ  ሪዘርቪየር 2500 ሜትር ኪዩብ ውኃ የመያዝ አቅም ያለው  ነው። ሰላሳ ዓመት ድሬን ውኃ ያጠጣ ባለውታዋ ነው የሚሉት አቶ ንጉሱ ያሁኖቹ  ሶስት አዳዲስ  ሪዘርቪየሮች  እያንዳንዳቸው 4000 ሜትር ኪዩብ  ውኃ የሚይዙ   መሆናቸውን አጫውተውናል። አዳዲሶች የውኃ ጉድጓዶች  45 ሊትር ውኃ  በሰከንድ የማመንጨት አቅም ያላቸው ሲሆን  እዚህን ሪዘርቪየሮች የሚያጠራቅሙት ውኃ   ከዘጠኝ ጉድጓዶች የሚሰበሰብ  ነው።

ምንም እንኳ ድሬዳዋ  ሞቃታማና ደረቃማ ብትሆንም  በከርሰ ምድር  ውኃ ሃብታም መሆኗን በከተማዋ  የመጠጥ ውኃ ፕሮጀክቶች   ጉዳጓዶች    አካባቢ በመሄድ መመልከት   በቂ ነው።   ድሬዳዋ   በከተማዋ ባንዱ ጫፍ   ጉድጓዶች በተቆፈሩባቸው አካባቢዎች  ሆኜ ድሬን ግራና ቀኙን  ተመለከትኩ። እውነትም በዙሪያዋ ያሉት ከፍተኛ  ቦታዎች የሚያፈሱት ውኃ  የትም አይደርስም ።  ምንም እንኳ የከርሰ ምድር የተሟላ  እውቀት  ባይኖረኝም   ስመለከት ግን ዝቅተኛ ቦታ ላይ ውኃ  መስረጉ  አይቀርም ና ግምቴ ልክ ሆኖ አገኘሁት። በግምት ለብዙ ህዝብ የሚደርስን ፅሁፍ ይዤ መቅረብ የሙያዬ ስነ- ምግባር ስለማይፈቅድልኝ  ከባለሙያ ማረጋገጥ ነበረብኝና  በባለስልጣኑ የውኃና ፍሳሽ ባለሙያውን   አቶ ንጉሴን አነጋገርኳቸው።

<<የድሬዳዋ የከርሰ ምድር ውኃዋ እንዴት ይገለጻል>> አልኳቸው። <<አንተ ሙቀቱን አይተህ ምናልባት  ውኃ ላይኖር ይችላል  ብለህ ገምተህ ሊሆን ይችላል። እውነታው ግን ድሬዳዋ  የከርሰ ምድር  ውሃ ሃብታም ነች። ከለማ እንኳን ለድሬዳዋ ህዝብ ለሌላም ይተርፋል።  የሃረር የመጠጥ ውኃ የተወሰደው ከድሬዳዋ  ነው። እንዳውም ና ላሳይህ>> ብለው  ድሬዳዋ መግቢያ ላይ የተዘረጋውን ለሃረር  ከድሬዳዋ ውኃ  የተላከላትን  ውኃ አሳይተውኝ ግምቴን እውነት አድርገውልኛል።

ይህንኑ የመጠጥ ውኃ ለዚህ ግብዓት በሚሆን መንገድ ምልከታ ሳደርግ አንድ ቀን ድሬዳዋ አዳራችንን እዛው አድርገን ነበር። እግረ መንገዳችንን አሁን ያለው የውኃ አቅርቦት ምን ይመስል ይሆን ብለን አንድ  ግለሰብ  አነጋገርን።

የጠየቅናቸው ግለሰብ ሆቴል አከራይተው  የሚተዳደሩ  ናቸው።  እያወጋን መሽቶ ነበርና እዛው ሆቴል አልጋ ያዝን ። ቀድሞ መግቢያ ቀዳዳዋን ሳይቀር የሚያውቀው ሾፌራችን  ይሄ እኮ የድሬ ጫፍ ነው አለን። እኔ ምን ቸገረኝ  ማደር ከቻልኩ

ብየው  አልጋ አሳይተውን    ስለወደድነው  ተከራይተን አዳራችንን እዛው አደረግን። ሴትዮዋን  <<ጠጋ አልኩ ና ሻወር አለ>> አልኳት  ።

መልሷ <<አዎን>> የሚል ነበር።

መኪናችንን ጥግ አስይዘን   ለስራችን የሚሆነንን ግብዓት በያዝነው  ክፍል  አስቀምጠን ከተማዋን በእግራችን ዘወር ዘወር እያልን ማየት ጀመርን።ድሬዳዋ ቀን ላይ በሙቀትና በወበቅ ቆንጠጥ ያደገችውን  መጤም ሆነ ነዋሪ ማታ መንፈሰን የሚያድስ አየር እንዲምግ ታደርገዋለች። እኛም ከድሬዳዋ አየር ለትዝታም ያክል ቢሆን ሙቅ አይሉት ቀዝቃዛ አየር ምገን   አልጋ ከተከራየንበት አካባቢ አመራን።

ሙቀትና ድካም የዋለበት ገላ ላይ ውኃ ማፍሰስ (ሻወር መውሰድ  ) ያባት ነው ብዬ ሻወር  ቤት ብገባ  እንኳን የምታጠብበት  ውኃ ላገኝ ለራሱ ሻወር ቤቱ  ውኃ ናፍቆታል።

<<ውኃ የለም እንደ>> ስል  አልጋ አከራየዋን ጠየቅኳት ።

<<ላመጣልህ ነው>> ብላ ተፍተፍ ማለት ጀመረች። ከየት ነው የምታመጣልኝ ብዬ ምናልባት  ከዋናው መስመር ተዘግቶ ይሆናል እያልኩ ስጠብቅ በባልዲ ውኃ መጣልኝ። መሃል አገር ቢሆን ግን  <<ውኃ ከሌለ ምን ይጠበስ>>፤<< ውኃ መጥፋት  ብርቅ ነው>> ብለው ያሳርፉኝ ነበር ብዬ አሰብኩ ። በዝናም ቢሆን ድሬዎች  እንግዳ ተቀባይ ናቸው የሚል  ወሬ ሰምቼ ስለነበር  መጠበቅ  ነበረብኝ። እውነት ነው  እንግዳ ተቀባይ መሆናቸውን  እኔም ምስክር ነኝ።

እግረ መንገዴን ለስራዬ  የሚሆን ጥያቄ ጠየቅኳት።<< ድሬዳዋ ውኃ ስትመጣ ተሻምተህ ትቀዳለህ  እስካላለቀ ድረስ ለሚመጣው ትሰጣለህ፤ ውኃ በፈረቃ ነው፤ ዞን አንድ ካገኘ ዞን ሁለት አያገኝም።አንተ ሻወር አለ ብዬህ ውኃ ሳመጣልህ እንደዋሸሁህ የቆጠርከው ባዲስ አበባ አይን አይተኸው ነው>> አለችኝ።

<<በድሬዳዋ ሻወር   አለ የሚባለው በሻወሩ ማውረጃ በኩል ሲመጣ ሳይሆን  ያጠራቀምከው  ውኃ እስካለህ ድረስ ነው፤እንደሌለው   የሚቆጠረው ደግሞ  ያጠራቀምከው  ውኃ ያለቀ ዕለት ነው>> የሚል ግልፅ  ምላሽ ሰጠችኝ።

የከተማ አስተዳደሩ  ይህን ችግር ለመፍታት  ምን እየሰራ ነው ስል ላቀረብኩላት ጥያቄ  <<በዚህ ታች የሚቆፍሩት ነገር አለ፤ የውኃ ስራ መሆኑን ሰምቻለሁ። ለልጆቻችን ይደርስ እንደሆነ እንጅ በዚህ አካሄድ ለኛ የሚደርስ አይመስልም>>  ሲሉ የፕሮጀክቶቹን ካንዴም ሁለቴ መዘግየታቸውን በባለሙያው  የተገለፀውም  ነዋሪዋም  ገለፁልኝ።

ይሄን  ፕሮጀክት ያስጀመራችሁ ቀጣይ ፍላጎት ብቻ አይመስለኝም፤ አሁናዊው የውኃው  አቅርቦታችሁ ምን ይመስላል ለሚለው ጥያቄዬ የተሠጠኝ መልስ  ከነዋሪዋ አስተያየት ጋር የሚመሳሰል ነው።

ነዋሪው ውኃ የሚያገኘው በፈረቃ ነው፤ አሁን የምንገነባው ግንባታ ያሁኑን ችግር ከመፍታቱም ባሻገር እስከ ቀጣይ እ.ኤ.አ. 2030 ዓ/ም ድረስ ለሚኖረው ፍላጎት ምላሽ የሚሰጥ ነው ሲሉ ችግሩ የሚፈታው ግን  ፕሮጀክቶቹ  ሲጠናቀቁ መሆኑን  ይገልፃሉ።

በአጠቃላይ  በድሬዳዋ  እየተገነቡ ያሉ የመጠጥ ውኃ ፕሮጀክቶች ቀጣዩን የህብረተሰቡን የመጠጥ ውኃ  ፍላጎቶች በመመለስ ረገድ  እምነት የሚጣልባቸው ቢመስሉም አሁንም የኤሌክትሮ መካኒካል ስራዎቹ ገና  የግዥ ማዘዣ  የተጻፈላቸው  እንጅ ብዙ ሂደቶችን ያላለፉ በመሆናቸው በጥር ወር ደርሰው ለህብረተሱ የውኃ ጥያቄ ምላሽ የሚሰጡ አይመስሉም።

ከበፊቱ  የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ  በመጨመር ላይ ያለውን የመጠጥ ውኃ ፍላጎትና አቅርቦት  የማቀራረብ ስራ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ውኃና ፍሳሽ ባለስልጣንን የሚጠብቀው  ትልቅ የቤት ስራ ነው።  ይህንን  የቤት ስራ  ፍላጎትና አቅርቦትን አመጣጥኖ የወ/ሮ ሰላምንንና የመሰሎቿን የሕብረተሰብ ክፍሎችን  ጥያቄ በመመለስ  ወደ ወሳኝ ምዕራፍ ያሸጋግራዋል እላለሁ!   ምስጋና፦ በመስክ ምልከታዬና አርቲክል በማዘጋጅበት ወቅት ዘወትራዊ እንግዳ ተቀባይነታቸው ላይ ከስራ ውጪ በተለይም በእሁድ ቀን  ከቤተሰባቸው እኩል ቆጥረው   ጊዜና ሁኔታ ባልገደበው ደግነት  ለዚህ ፅሁፍ ግብዓት ለሰጡኝ ለአቶ ንጉሱ መንግስቴ። እንኳን መጣሁ ድሬ አስብላችሁኛል። አበቃሁ!